# ተዓምረ ብርሃኑ

ገረመው ዘከአብ

እውነት እውነት እላችኋለሁ

ጆሮ ያለው ይዝጋው፤ አይን ያለው ይሸፍነው

ይህን በአድናቆት ተዓምረ ብርሃኑ ትሉት ዘንድ ተፈቅዷል ፡፡

ፈሪሳውያንና ጸረ ግንቦቶች በሞላ ሲነዙ የከረሙት ሐሜት ሁሉ ከሸፈ፡፡

ሳያዩ የሚያምኑ ብጹዓን ናቸው፡፡

በስድስት ወር አዲስ አበባ እናደርሳችኋለን ያልነውን አምነው ገንዘብ የተበሉ ዛሬም ማመናቸው ታማኝ ምዕመናን ያደርጋቸዋል፡፡

እውነት እውነት እላችኋለሁ ተዓምረ ብርሃኑ ታይቷልና ተቀበሉት፡፡

ሙቶ የማይሞላ ጦር በሺዎች የታጠረውን ድንበር ጥሶና በርግዶ ገብቷል፡፡

ከቃፍቲያ ወልቃይት እስከ አርማጪሆ መተማና አዘዞ ጉዞው 15 ቀን ብቻ ፈጅቷል ፡፡

ሕዝቡ ኪራራይሶ ብሎ አደነቀ ፡፡

አዘዞ ከጎንደር ሰባት ኪሎሜትር ርቀት ስለሆነ ቀጣዩ የጥቃት ሰለባችን ጎንደር ይሆናል ፡፡

ረፍርፈን አቁስለን ምርኮ ግን አጥተናል ፡፡

ሰው ሁሉ እጹብ ድንቅ አለ ፡፡

መሪያችው ፈሪ ነው እንኳን በግንባር በአህጉሩም አይታይ ያሉ አፈሩ፡፡

ከመቅጽበት ያውም መሄዱን አውጆ ላስ ብሎ አስመራ ገባ ፡፡

ጥቂቶች ብቻ ተቀበሉት፡፡ አቶ ኒአሚንም ከነከተማ ልብሱና መጫሚያው በረሀ ነኝ ብሎ ተቀበለው፡፡ ቀደም የሄደው የጦር መሪም በረሃ በተባለ ቦታ ነጭ ሸሚዙን፤ሱፍ ሱሪውን ለብሶ ተቀባይ አስተናጋጅ ሆነ፡፡

ዊስኪው ተቀዳ፤በጠረጴዛ ዙሪያም እንጀራ በወጥ ተበላ ፡፡ አዲሱን በረሀ ሕዝብ ሁሉ አይቶ ተገረመ ፡፡

ማነው መጣሁ ብሎ ጮሆና አስጨሆ የሌላን ሀገር ከተማ የጦር ሜዳ ብሎ በድፍረት የሚያቀርበው? ይህ ተዓምር አይደለምን?

ጀሌዎችም ተዓምር ሰሪው ከአስመራ ወደ አዲስ አበባ ሲስፈነጠር ታያቸው ፡፡

እምነታቸው ያመረቃል ፡፡

ተንከሎኞች ደግሞ ተዓምረኛው ወደ ሞቀ ቤቱ ላይመለስ ምሏል ብለው ጻፉ ፡፡

ፈሪሳውያንና ሮማውያን ተዓምር ስራ ብለው ኢየሱስን እንዳስጨነቁት ነው ፡፡

የጥይት ድምጽን የሚፈራ የጦር መሪ አይሆንም ፡፡

ዓመታት ወስዶ የተገነባ ቦርጭም ለበረሃ እንቅስቃሴ ከቶም አያመችም ፡፡

መሃይሞች ይህን ይረዱ ዘንድ ጥሪ ተደረገላቸው ።

ይህን በወረቀት ከቃፍቲያ ወደ ጎንደር ዙሪያ የደረሰ ጦር በወረቀት እንዴትስ ይመልሰው ይሆን ብለው ጀሌዎች ተጨነቁ።

ተአምረ ብርሃኑን በጉጉት ጠበቁ ።

ዓይን ያለው ይሸፍን ሲልም አዘዛቸው ።

ኤርትራን የኢትዮጵያ የትግል ሜዳ ካላችሁ ሌላውን ማመን አይከብድም አላቸው ።

ሁመራን አጥቅተን ብዙ ወታደር ገደልን ያልነውን ሳትስቁ ካመናችሁ ሌላው ሁሉ ቀላል ነው አላቸው ።

ወያኔ ሳይከታተለን ሳይወጋን ወደ አርማጩሆ ዘለቅን ስንል ካመናችሁ ይህን ማመን አይከብድም አላቸው።

ጦሩ ተመለስ ብሎ ተማጸነኝ ብሎ ሳይውል ሳያድር ዋሺንግተን ሲገባ አወይ ውሸት ባዮች ቂቶች መሆናቸው አይቀርም ።

ይህ ግን አያስፈራኝም ሲል ደረቱን ሞልቶ ተናገረ ። አሞኙኝ ባይ ዳያስፖራ ነውና ብሎም ተሳለቀ።

የጥይት ድምጽ የሚፈራ አዋጊ እንዴት ሊሆን ይችላል? እንዴትስ ለመስዋዕትነት ራሱን ይዳርጋል?

ወደ ቤቴ መመለሴማ አይቀርም አላችው ። ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ እግዚኦ አቆያለሁ ያለው ውሸቱ ብለው አደነቁ!

ጦሩንም በዘዴ በምትሃት ፈጥሬ እንዳሰማራሁት በዘዴ በወረቀት እመልሰዋለሁ ወደ ካምፑ ብሎ አረጋጋቸው ።

ግዳጃችሁ እጃችሁን መፍታትና ገንዘብ ወደ እኔ ማጉረፍ ነው አላቸው።

ሞኝና ገንዘቡ ቶሎ ይለያያሉ ተብሎ የል ?

ንዋይ አይወድም ሲሉ የነበሩትም አፈሩ ።

ወደ አዲስ አበባ ሰሞኑን እንጠራለን ብለው ያለሙትም አንገት ደፉ ።

ተዓምረኛው ተወንጫፊ ጦር ለምንስ አዲስ አበባ ራቀው ብለው ተገረሙ ።

ውድቀታችንን ታያላችሁ፤ስንነሳም ታያላችሁ ብሎ ነገራቸው። ብዙዎች ግን መርዶውን አልተረዱትም ።

ለሽምቅ ውጊያ አዲስ ይዘት ሰጠነው አላቸው ። ከሮኬት የፈጠነ ተወንጫፊ ጦር ።

መዋሸት ባልቻሉትም ላይ ሁሉም ተሳለቁ ።

ምድረ ሀበሻ፤ወዲ ክፍሌ፤ ዘ ሙሴ ተባዮች ሁሉ በክህደታቸው ተጋለጡ ።

እውነት እውነት እላችኋለሁ ፤

ሳያዩ የሚያምኑ፤ነጋ ጠባ የሚታለሉ፤ውሸት ነው ሲባሉ ሀቅ ነው የሚሉ ብጹዓን ናቸው ።

ተአምረ ብርሃኑ ዓይናቸውን ያበራላቸዋል፤ ሀጢያት ጋባዥ ከሆነው ሰይጣናዊ ንዋይም ያላቅቃቸዋል ።

እውነት እውነት እላችኋለሁ።

ሜዳ ስል ኢርትራን ነው። ሱፍ ለብሶ በጠረጴኢዛ ዙሪያ ማዕድ የበረሃ አይደለም ።

አልመለስም አለ የሚሉት ግን ጠላቶቼ ናቸው ። በሄድኩበት ሊያስቀሩኝ ፈላጊዎች ።

ያመኑኝ ይጸድቃሉ።

ከጽድቅ በላይ ድል ይጣፍጣል? ሀቅ ይጥማል?

ዛሬ የደመቀው ወሬ ነገ እንደ ጠዋት ጤዛ ይተናል ።

ይህን ያለረዱ ቢጎዱ ጥፋቱ የራሳቸው ነው ።

ተዓምረ ብርሃኑ ሞኝ እስካለ ይቀጥላል ።